# "ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስናልፍ ኢትዮጵያ ነን"

**ይልቃል ፍርዱ** 04-11-18

ኢሕአዴግ በአዲስ ምእራፍ ጉዞ ጀምሯል፡፡በሀገር ደረጃ ተከስቶ የነበረው የሰላምና አለመረጋጋት እጦት በብዙ መልኩ በሀገራችን ላይ ችግር የጋረጠ ነበር፡፡ የዜጎች ሕይወት አልፏል፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ የመንግስት፣ የሕዝብና የግለሰቦች ንብረት ወድሟል፡፡ ይህ አሳዛኝ ክስተት በተለይም የሰላም መደፍረስና እጦት በሕዝብ ውስጥ ከፍተኛ ስጋትና ጥርጣሬ ፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ዛሬ የሰላም አየር በመላው ሀገሪቱ እየነፈሰ ይገኛል፡፡ አዎን ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስናልፍ ኢትዮጵያ ነን፡፡ ስንኖር በመሬቷ ላይ ስናልፍ ደግሞ ከመሬቷ ስር ነን፡፡

ኢሕአዴግ የመረጣቸው አዲሱ የድርጅቱ ሊቀመንበርና ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አሕመድ በፓርላማ ቃለመሀላ በፈጸሙበት ወቅት ባደረጉት ድንቅ ታሪካዊ ንግግር በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ቀልብና ልቦና አሸንፈው በእምባም አራጭተው አዲስ ብሔራዊ የሀገር ፍቅር መንፈስ እንዲያንሰራራ ማድረግ ችለዋል፡፡ ኢሕአዴግ በአዲስ መልክ በአዲስ ትንሳኤ ሀገር መምራቱን ቀጥሏል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ስሜት ኮርኳሪ ከመሆንም ባለፈ በጥልቅ ሰብዓዊነትና ሀገራዊ አክብሮት የተሞላ በመሆኑ ሁሉንም ወገን ከጫፍ ጫፍ ማነቃነቅ የቻለ ነበር፡፡

በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት ባልተለመደ ሁኔታ ፓርላማውን ይቅርታ ጠይቀው ስለእናታቸው ያደረጉት ንግግር "የመላውን ኢትዮጵያ እናቶች ባሕርይ የምትወክል ቅን ደግ ቁሳዊ ሀብትም ሆነ የዘመኑ እውቀት የሌላት እናቴ ዛሬ ከጎኔ ባትኖርም ብዙዎችን እናቶች እንደምትወክል ስለሚሰማኝ ለሁሉም ክብር ይድረስ ነፍሷን ፈጣሪ በአጸደ ነፍስ ያኑርልኝ፤የእሷ ምትክ ሁና ከጎኔ ለቆመችው ባለቤቴም አክብሮቴን መግለጽ እወዳለሁ" የሚለው ንግግራቸው ለእናቶችና ለሚስቶች በአጠቃላይ ለሴቶች ታላቅ አክብሮት የሰጠ ጥልቅ ሰብዓዊነትን የያዘ ከመሆኑ የተነሳ ስርጭቱን በየቦታውና በያለበት የሚከታተለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በእንባ እንዲራጭ አድርጓል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ በእምባ ያራጨን ንግግራቸው ስለእናት የተናገሩት ብቻ አይደለም፡፡ በክፉም በደጉም በደስታውም በሀዘኑም ሳንለያይ በአንድነታችን ውስጥ ባለው ልዩነት ውስጥም ዘመናትን የተሻገርን የብዙ ትውልድ መስዋእትነት ያጸናት የጋራ ቤታችን ስለሆነችው ኢትዮጵያ ደግመው ደጋግመው በአጽንኦት የገለጹት ንግግርም ተስፋ በቆረጠ ሕዝብ ውስጥ ነፍስ የዘራ ጨለማን የገፈፈ ዳግም ተስፋን ያጫረ ነበር፡፡

በሙስና፣ በኪራይ ሰብሳቢዎች፣ በመልካም አስተዳደርና በፍትሕ እጦት ችግር ተንገፍግፎ ለነበረው ሕዝብ ታላቅ ተስፋን የሰነቀ ለውጥ ኢሕአዴግ እንደሚያመጣ እምነት አሳድሯል፡፡ ኢሕአዴግ ከገባበት አጣብቂኝና ውስብስብ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግር መውጫ መንገዱን በትክክል አግኝቷል፡፡ በመሆኑም "እምነት ጥሎ የመረጠኝና ለዚህ ያበቃኝን ድርጅቴን ኢሕአዴግንና የሀገሬን ሕዝብ አመሰግናለሁ ነው ያሉት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አቢይ አሕመድ፡፡

በእርግጥም ዶ/ር አቢይን ከተራ ወታደርነት ጀምሮ ደረጃ በደረጃ እስከ ኮሎኔልነት ያደረሰው፤ ከቢኤዲግሪ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ያበቃቸው፣ በተለያዩ ከፍተኛ መንግስታዊ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሕዝብን እንዲያገለግሉ የሾማቸው እና የመረጣቸው ድርጅታቸው ኢሕአዴግ በመሆኑ ከመነሻው ጀምሮ የኢሕአዴግ ልጅ ናቸው፡፡ አዲስ ለውጥ

ለማምጣት የሕዝብን መንፈስ በአንድ ለማቆም የቻለ ሰው መፍጠር በመቻሉ በዚህ ድርጅቱ ሊኮራበት ይገባል። ኢሕአዴግንም እንደ ድርጅት ጥንካሬውን ያሳያል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ በዚህ ከፍተኛ ሀገራዊ የኃላፊነት ቦታ ሁነው ስራ ሲጀመሩ ሕዝብ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ታላቅ ተስፋን ሰንቆ በሀገራችን ሰላም፣ ፍቅር፣ መግባባት፣ እኩልነትና ፍትሕ ሰፍኖ ሰብአዊ መብት እንዲከበር ያለውን ጥልቅ ስሜትና ምኞት ገልጿል። እየገለጸም ይገኛል።

የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሚል የጠሯቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ በሀገራዊ ጉዳይ ይበጃል በሚሉት አጀንዳ ዙሪያ በወንድማማችነት ስሜት ለመነጋገር መንግስታቸው ያለውን ጽኑ ፍላጎት ገልጸዋል። ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን መንግስታቸው ጠንክሮ እንደሚታገል ሲገልጹ <የሀገር ሀብት ለሁሉም ይበቃል፤ ሀገር ጥቂቶች የሚዘርፉት ሀብት ግን የላትም> የሚለውን የሕንዱን የነጻነት ትግል መሪ ጋንዲን አባባል ደግመው አንጸባርቀዋል። ይህ ጥልቅ ንግግር በሕዝቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ጠፍቶና ተዳፍኖ የቆየውን ሳይሰራበት የኖረውን ብሔራዊ የሀገር ፍቅር ስሜት ከመቃብር ፈንቅሎ ለማውጣት የቻለ ነው,።

የብሔር ብሔረሰቦችን ጥንትም በሀገራችን ተጠብቆና ተከብሮ ተሳስሮ የኖረ አንድነት በማይበጠስ ገመድ የተገመደ በመሆኑ አብረን ከመሆን ሕመማችንን በጋራ ከመታመም አብረንም ከመዳን አብረን በመነጋገር መፍትሄ ከማበጀት ውጭ ተለያይተን መቀጠል የማንችል መሆኑን በአጽንኦት ገልጸዋል ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ።

ለዚህ ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር ማሳያ አድርገው ያነሱት "አማራው በካራማራ ጦርነት ለኢትዮጵያ አንድነትና ክብር ተዋግቶ ከካራማራ አፈር ጋር ተቀላቅሏል፤ትግራያውያን በመተማ ከሀገሬ በፊት ብሎ አንገቱን ሰጥቶ የመተማ አፈር ሆኗል፤ ኦሮሞው ለሀገሩ ክብር አድዋ ዘምቶ ተዋግቶ ከአድዋ አፈር ጋር ተቀላቅሏል።" አንድ አዛውንት አባት የተናገሩትን በማስታወስ <ስንኖር ሰው ስንሞት አፈር ቀጥሎም ሀገር እንሆናለን> ያሉትን አንስተዋል።

በካራማራው ታሪካዊ ንግግር የሚታወስ ግዙፍ ታሪክ አለ።ሁሉም ኢትዮጵያዊ ታላቅ ተጋድሎ ያደረገበት ነው።በታላቅ መስዋእትነት የሶማሊያውን ወራሪ ሠራዊት ከኢትዮጵያ ግዛት ጠራርጎ በማስወጣት የመጨረሻውን ድል ያወጀው በካራማራ ተራራ ነው። የሶማሊያው መሪ የነበረው ጄነራል ዚያድ ባሬ በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ኃይለስላሴ ከስልጣን ወርደው ወታደራዊው መንግስት ስልጣን በያዘበት ወቅት ኢትዮጵያ ተዳክማለች መውረር ያለብኝ ግዜው አሁን ነው በሚል በሀገራችን ላይ ግዙፍ ወረራ አካሄደ።

23 ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቁ እግረኛ ክፍለጦሮችን (አንድ ክፍለጦር በወቅቱ አስር ሺሕ ሠራዊት ይይዝ ነበር) 239 ሺህ እግረኛ ሠራዊት ማለት ነው። ረዥም ርቀት የሚደበድቡ መድፎችን፣ ቢኤሞችን፣ በርካታ ዘመናዊ የታንከኛ፣ የመድፈኛ፣ የአየር መቃወሚያ ምድቦችን እና በአየር ላይ የሶቪየት ስሪት የሆኑ ተዋጊ ጀቶችን በማሰማራት በየድንበሩ የነበሩ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የኢትዮጵያ ሠራዊትና የፖሊስ ኃይል እየደመሰሰ ሕዝቡንም እየጨፈጨፈ የኢትዮጵያን ግዛት 700 ኪሎ ሜትር ጥሶ የገባበት ግዙፍ የወረራ ታሪክ ነው። መረጃ በመስጠት መንገድ መሪ በመሆን ያገለገሉት በኢትዮጵያ ተወልደው ያደጉ የሶማሌ ተወላጆች ነበሩ። ዛሬም ሕዝቡ ይህንኑ እውነት ይመሰክራል።

በዚህ መልኩ የኢትዮጵያ ሠራዊት በወቅቱ የነበረው የሰው ኃይልና ከባድ መሳሪያ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በቀላሉ ነበር ገስግሶ ብዙ ቦታዎችን የተቆጣጠረው። በቀድሞው ምስራቅ ኢትዮጵያ በዛሬው አገላለጽ ኦሮሚያ ነዋሪ የሆኑትን የኦሮሞ ተወላጅ አርሶ አደሮችን የሶማሊያ ሠራዊት በግፍ ጨፍጭፏል። ለከፋ እሥርም ዳርጓል።

በዚህ ጦርነት ሶቪየት ሕብረት ለኢትዮዮጵያ ከፍተኛ የጦር መሳሪያ ረድታለች።በተለይ ኩባ ተዋጊ ሠራዊቷን በቀጥታ ከኢትዮጵያ ጎን ተሰልፎ እንዲዋጋ በማድረግ በታላቅ ጀግንነት ለኢትዮጵያ ክብር ሲዋደቁ ከ120 በላይ የኩባ ተዋጊዎች የሕይወት መስዋእትነት ከፍለዋል። የመናውያንም ለኢትዮጵያ ክብር ተዋግተዋል። ግዛቴ እስከ አዋሽ ነው በሚል እብሪት የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ 700 ኪሎሜትር በመግባት በወረራ በርካታ መሬቶችን ተቆጣጥሮ ሕዝቧን የጨፈጨፈውን የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ከግዛታችን ለማስወጣት ከ300 ሺህ በላይ ሚሊሺያ ሠራዊት ከመላው ኢትዮጵያ ተውጣጥቶ በአጭር ስልጠና በመደበኛ ሠራዊቱ መሪነት ወደ አውደ ውጊያ ገብቶ ግዛቱን ነጻ ማውጣት ችሏል።

በወረራ የተያዙትን ግዛቶቻችንን ለማስለቀቅ በተለያዩ አቅጣጫዎች በተደረገው ውጊያ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መስዋእትነት ተከፍሎ የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት በየቦታው ተደመሰሰ።ተማረከ። የኢትዮጵያ አየር ኃይል በነበሩት ጥቂት ሚግ አምስት ተዋጊ ጀቶች በሶማሊያ ሠራዊት ላይ ታላቅ ጀግንነት መፈጸም ተችሏል። በተጨማሪም የድርጅትና የስንቅ መስመሮቹን ከማውደም ባለፈ በአስደናቂ ብቃት አየር ለአየር በተደረገው ፈታኝ ውጊያ በርካታ የሶማሌ ጀቶችን በማጋየት ጀግንነቱን አስመስክሯል።

የሰማሊያ ወራሪ ሠራዊት በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛት ተደምስሶ አፈር ሆኖ ሲቀርና የሸሸው ሲሸሽ የመጨረሻው ምሽግ የነበረው የካራማራ ተራራም በኢትዮጵያውያን ታላቅ ጀግንነትና ተጋድሎ ነጻ ወጣ። የሞተው ሞቶ በርካታ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ተማረኩ። ይህ ከመላው ኢትዮጵያ ከሰሜን፣ ከመሀል፣ ከምእራብ፣ ከደቡብና ከምስራቅ ተውጣጥቶ የተሰለፈው ተዋጊ ሠራዊት ሁሉንም የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች ያካተተና ያቀፈ ሲሆን ድሉ የመላው ኢትዮጵያውያን ታላቅ ድል ነው።

ከኢጣሊያ ጋር በአድዋ ካደረግነው ጦርነትና ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኃላም የተደረገ ሀገርን ከወራሪ የመከላከልና የማስከበር ግዙፍ ጦርነት ነበር።በአግባቡ ሳይዘከር ብዙ አመታት ያለፉ ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ በመንግስት ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ በማድረጋቸው ታሪኩን በቅርብ በሚያውቀው ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትና ድጋፍ አስገኝቷል። ይህ ግዙፍ ሀገራዊ ድልና ጀግንነት ብዙም ሳይነገርለት ሳይዘከር በርካታ አመታት ተቆጥረው የነበረ ቢሆንም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ ይህንን የኢትዮጵያውያን ድል እውቅና ሰጥተው ዘክረውታል።